www.ethiopianorthodox.org

መጻሕፍተ ፡ መነኮሳት ፨

አንደኛ ፡ መጽሐፍ ።

# ማር ይስሐቅ

ከቀድሞ ፡ አባቶች ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሊቃውንት ፡
ሲያያዝ ፡ የመጣውን ፡ ንባባቸውንና ፡ ትርጓሜያቸውን ፡
በአንድነት ፡ አድርጐ ፡ ተስፋ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡
ዘሀገረ ፡ ቡልጋ ፡ አዘጋጀው ።

በተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት
፲፱፻፸፱ ፡ ዓ. ም. ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org



ል ። የማር ፡ ይሰሐቅ ፡ እስመ ፡ ቢመች ፡ ይፈቱታል ፡ ባይመች ፡ ይተውታል ፡ ብለው ፡ አዋጅ ፡ ይነግሩለታል ።

ወለብእሲ ፡ ዘይፈቅድ ፡ ረኪበ ፡ ምግባራት ፡ መንፈሳውያት ፡ በፍድፋዴ ፡ ዘብዙኅ ፡ ወዘዕሙቅ ።

ምግባር ፡ ትሩፋትን ፡ በመስራት ፡ ረቂቅ ፡ የሚሆኑ ፡ ሀብታት ፡ ምሥጢራትን ፡ ሊያገኝ ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፤ እንድም ፡ ጸጋ ፡ ክብር ፡ ለማግኘት ፡ ምግባር ፡ ትሩፋትን ፡ አብዝቶ ፡ መስራት ፡ የሚወድ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ።

ይደልዎ ፡ ቅድመ ፡ ይትናከር ፡ እምነ ፡ ዓለም ።

አስቀድሞ ፡ ከዓለማዊ ፡ ሥራ ፡ መለየት ፡ ይገባዋል ።

እርእያ ፡ ሕፃን ፡ ዘጎደገ ፡ ጥበ ፡ እሙ ።

የናቱን ፡ ጡት ፡ እንደ ፡ ተወ ፡ ሕፃን ።

እስመ ፡ ግብር ፡ ሥጋዊ ፡ ይቀድሞ ፡ ለነፍሳዊ ።

ትሩፋተ ፡ ሥጋ ፡ ከትሩፋተ ፡ ነፍስ ፡ ይቀድማልና ።

በከመ ፡ ቀደመ ፡ መሬት ፡ እምነ ፡ ነፍስ ፡ እንተ ፡ ተነፍሐት ፡ ውስተ ፡ ገጹ ፡ ለአዳም ።

በአዳም ፡ አድራ ፡ ካለች ፡ ከተፈጥሮተ ፡ ነፍስ ፡ ተፈጥሮተ ፡ ሥጋ ፡ እንደቀደመ ። የነፍስ ፡ ተፈጥሮ ፡ ግብር ፡ እምግብር ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ ከመታየት ። እስመ ፡ ሰዓለ ፡ ሰማይ ፡ ቀዳማዊ ፡ እንዲል ። እምኅበ ፡ አልቦ ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ የተመቸ ።

ዘኢያጥረየ ፡ ግብረ ፡ ሥጋዊ ፡ አይትክሃሎ ፡ አስተጋብኦ ፡ ግብር ፡ መንፈሳዊ ።

ትሩፋተ ፡ ሥጋን ፡ ያልሰራ ፡ ትሩፋተ ፡ ነፍስን ፡ መስራት ፡ አይቻለውም ።

እስመ ፡ ዘቲ ፡ ትትወለድ ፡ እምእንታክቲ ።

ትሩፋተ ፡ ነፍስ ፡ ከትሩፋተ ፡ ሥጋ ፡ ትገኛለችና ።

በከመ ፡ ሰዊት ፡ ይትወለድ ፡ እምነ ፡ ዕራቁ ፡ ሕጠት ።

ሰዊት ፡ ከፍሬው ፡ ብቻ ፡ እንዲገኝ ። ሰዊት ፡ የሚለው ፡ ብቻ ፡ እሸት ፡ አይደለም ፡ ግንዱም ፡ ቅጠሉም ፡ ሰዊት ፡ ይባላል ።

ወዘአልቦቱ ፡ ምግባር ፡ ነፍሳዊ ፡ ናሁ ፡ የኃጉሎ ፡ ለሀብት ፡ መንፈሳዊ ።

ትሩፋተ ፡ ነፍስ ፡ የሌለው ፡ ሰው ፡ ጸጋ ፡ አያገኝም ።

እስመ ፡ ድካማት ፡ እለ ፡ ሀለዋ ፡ በዝንቱ ፡ ዘመን ፡ ዘይእዜ ፡ በእንተ ፡ ጽድቅ ፡ ኢይትዔረያሁ ፡ ለተድላ ፡ ዘድልው ፡ ውስተ ፡ ሠናያት ፡ ለፀዋርያን ፡ ምንዳቤ ፡ ዘዝየ ።

ስለ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የሚቀበሏቸው ፡ መከራት ፡ የዚህን ፡ ዓለም ፡ መከራ ፡ ታግሠው ፡ ለሚቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ ተዘጋጅቶ ፡ ያለ ፡ የወዲያኛውን ፡ ዓለም ፡ ተድላ ፡ አይተካከሉትምና ።

በከመ ፡ ይትልዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይዘርኡ ፡ ዘርዐ ፡ አንብዕ ፡ ከዓስስተ ፡ ትፍሥሕት ።

እያዘኑ ፡ እየተሰቀቁ ፡ የሚዘሩ ፡ ሰዎች ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ እንዲያጭዱ ።

ከማሁ ፡ ይትልዎሙ ፡ ፍሥሐ ፡ ለፀዋርያን ፡ ምንዳቤ ፡ በእንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ።

እኒያን ፡ ደስ ፡ እንዳላቸው ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ብለው ፡ መከራ ፡ የሚቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ በወዲያው ፡ ዓለም ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

እስመ ፡ ሲሳይ ፡ ዘግቡር ፡ እምነ ፡ ሐፍ ፡ ይጥዕም ፡ ለሐረሳዊ ።

ጥሮ ፡ ግሮ ፡ የሚያገኙት ፡ ምግበ ፡ ጻን ፡ ገበሬውን ፡ ደስ ፡ ያሰኘዋል ። የፃረበት ፡ የጋረበት ፡ ነውና ። አንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ጣዕም ፡ አሳድሮበት ።

ወምግባራት ፡ እለ ፡ ይወጽኣ ፡ እምኅበ ፡ መስተጋድል ፡ በእንተ ፡ ርትዕ ፡ ያስተፌሥሕሁ ፡ ለልብ ፡ ዘይትዌከፍ ፡ አእምሮተ ፡ ክርስቶስ ፡ ይዕበይ ፡ ስሙ ።

ቅን ፡ ስለሆነ ፡ ከሚጋደል ፡ መነኰሴ ፡ የሚገኝ ፡ ትሩፋት ። አንድም ፡ እንተ ፡ ትመጽእ ፡ በእንተ ፡ ርትዕ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ። ቅን ፡ ስለሆነ ፡ ወደሚጋደል ፡ መነኰሴ ፡ የሚመጡ ፡ መከራት ፡ አንድም ፡ ቅን ፡ ስለሆነ ፡ ወደሚጋደል ፡ መነኰሴ ፡ የሚመጡ ፡ ሀብታት ፡ ስሙ ፡ ይክበርና ፡ ክርስቶስን ፡ ማወቅ ፡ ገንዘብ ፡ ያደረገ ፡ ልቡናን ፡ ደስ ፡ ያሰኙታል ።

ተዓገሥ ፡ ሶበ ፡ ይሳለቁከ ፡ ወይዘንጉጉከ ፡ በፈቃድ ፡ ኄርት ፡ በእንተ ፡ ኄሩት ።

በበጎ ፡ ፈቃድ ፡ ሳለህ ፡ የማይገባ ፡ ነገር ፡ ቢናገሩህ ፡ ታገሥ ። አንድም ፡ ተዓገሥ ፡ በፈቃድ ፡ ኄርት ፡ የማይገባ ፡ ነገር ፡ ቢናገሩህ ፡ በበጎ ፡ ፈቃድ ፡ ሁነህ ፡ ታገሥ ።

ከመ ፡ ትርከብ ፡ ሞገሰ ፡ በኅበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ።

ክብር ፡ ይግባውና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ባለሟልነትን ፡ ታገኝ ፡ ዘንድ ፡ ታገሥ ።

ኵሎ ፡ ቃለ ፡ ክቡደ ፡ ዘይትዔገሥ ፡ ሰብእ ፡ በአእምሮ ፡ ዘእንበለ ፡ ይፃእ ፡ እምኔሁ ፡ ቃለ ፡ ትዕቢት ፡ ወተዋሥኦ ።

ምነው ፡ እንዲህ ፡ አልኸኝ ፡ ሳይል ። አንድም ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ እንጂ ፡ እኔ ፡ አይደለሁም ፡ ሳይል ፡ በፈሊጥ ፡ ሁኖ ፡ ክቡዱን ፡ ነገር ፡ የሚታገሥ ፡ ሰው ።

በውእቱ ፡ ጊዜ ፡ ይትወደይ ፡ ዲበ ፡ ርእሱ ፡ አክሊለ ፡ ሦክ ።

ለጊዜው ፡ እንደሾህ ፡ ይሆንበታል ።

ወብፁዕ ፡ ውእቱ ።



ነገር ፡ ግን ፡ ብፁዕ ፡ ነው ። አንድም ፡ እንደ ፡ ጌታ ፡ አክሊለ ፡ ሦክ ፡ ይሆንለታል ። አንድም ፡ በአክሊለ ፡ ሦክ ፡ የሚገኝ ፡ ክብርን ፡ ያገኛል ። አንድም ፡ ጌታ ፡ አክሊለ ፡ ሦክን ፡ ታግሦ ፡ ያመጣውን ፡ ክብር ፡ ያገኛል ። ወብፁዕ ። ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ነው ።

እስመ ፡ ይትኬለል ፡ በጊዜ ፡ ኢተኀዘበ ፡ በአክሊል ፡ ዘኢይረክቦ ፡ ሙስና ።

ባልጠረጠረው ፡ ጊዜ ፡ በማያልፍ ፡ ክብር ፡ ይከብራልና ። ዝም ፡ ብሎ ፡ ስራውን ፡ ይሰራል ፡ እንጂ ፡ ክብሩ ፡ የሚገኝበትን ፡ ጊዜ ፡ አያውቀውምና ።

ዘይኅይይ ፡ እምተከብሮ ፡ በአእምሮቱ ፡ ዝንቱስ ፡ ናሁ ፡ አሠናያ ፡ ለነፍሱ ፡ ለተድላ ፡ ዓለም ፡ ዘሀለዋ ፡ ትምጻእ ።

በፈሊጥ ፡ ሁኖ ፡ አበ ፡ አበ ፡ ከመባል ፡ የተለየ ፡ ሰው ፡ ሰውነቱን ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ ላላት ፡ ለመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አበቃት ። አንድም ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያላት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ለሰውነቱ ፡ አዘጋጀ ። አንድም ፡ እአመራ ፡ በነፍሱ ። ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያላት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በሰውነቱ ፡ አወቃት ።

ዘሰ ፡ ይቤ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ገደፎ ፡ ለዓለም ።

ዓለምን ፡ ተውሁ ፡ ያለ ።

ወምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ይትበአሶሙ ፡ ለሰብእ ፡ በእንተ ፡ ምንትኒ ።

ዓለምን ፡ ተውሁ ፡ እያለ ፡ በማናቸውም ፡ ሰዎችን ፡ የሚጣላቸው ።

ከመ ፡ ኢትኅጽጽ ፡ ዕረፍቱ ፡ በምንትኒ ፡ ግብር ።

በማናቸውም ፡ ስራ ፡ ሆዱ ፡ እንዳይጐድል ።

ውእቱስ ፡ ድውይ ፡ ፍጹም ።

እንዲህ ፡ ያለው ፡ ፍጹም ፡ ድውይ ፡ ነው ።

እስመ ፡ ናሁ ፡ ገደፎ ፡ ለሥጋ ፡ ኵለንታሁ ፡ በፈቃደ ፡ ዚአሁ ፡ ወናሁ ፡ ይፃባዕ ፡ በእንተ ፡ ፩ዱ ፡ አባል ።

ፈጽሞ ፡ ዓለምን ፡ ተውሁ ፡ ብሎ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ አካል ፡ ይፃላልና ። ፩ዱ ፡ አባል ፡ የተባለ ፡ ሆድ ፡ ነው ። እባብ ፡ ግደል ፡ ከነበትሩ ፡ ገደል ፡ እንዲሉ ፡ ሬኤርሶ ፡ ካልተወው ፡ ምን ፡ ይረባዋል ፡ ምን ፡ ይጠቀመዋል ። እንደ ፡ ሽንኩርት ፡ መደብ ፡ መሆኑ ፡ ነውና ። ይህ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ይመስላል ፡ ቢሉ ፡ መላ ፡ አካሉን ፡ ነስተውት ፡ አንዱን ፡ አልሰጥም ፡ ብሎ ፡ የሚፃገር ፡ ሰውን ፡ ይመስላል ።

ዘይኅይይ ፡ እምዕረፍተ ፡ ዝንቱ ፡ ዓለም ፡ ናሁ ፡ ሐወጸ ፡ በልቡ ፡ ኀበ ፡ ዝኩ ፡ ዓለም ፡ ዘሀለዎ ፡ ይምጻእ ።

ከዚህ ዓለም ፡ ከተድላው ፡ ከደስታው ፡ የተለየ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ አወቀ ፡ በል ።

ወእሱርስ ፡ ያፈቅር ፡ ጥሪተ ።

በዚህ ፡ ዓለም ፡ ፍቅር ፡ የታሰረ ፡ ገንዘብ ፡ ይወዳል ።

እስመ ፡ ገብር ፡ ውእቱ ፡ ለሕማማት ።

ለኃጣውእ ፡ ተገዥ ፡ ነውና ።

ኢይምስልከ ፡ ኦፍቁር ፡ ከመ ፡ አጥርዮ ፡ ወርቅ ፡ ወብሩር ፡ ውእቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ፍቅረ ፡ ጥሪት ።

በገዳም ፡ ምን ፡ ወርቅ ፡ አለና ፡ እንዲህ ፡ ትላለህ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ። ገንዘብ ፡ የሚባል ፡ ወርቅ ፡ ብቻ ፡ አይምሰልህ ።

አላ ፡ ኵሉ ፡ ዘይስቀል ፡ ቦቱ ፡ ፍትወታቲከ ።

ፈቃድህ ፡ የተሳበበት ፡ የተጠለፈበት ፡ ሁሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ኢትንዓድ ፡ ለዘይፃሙ ፡ ፃማ ፡ ሥጋዊተ ።

ትሩፋተ ፡ ሥጋ ፡ በመስራት ፡ የሚደክም ፡ ሰውን ፡ ጣዕም ፡ ይቀምሳል ፡ ጸጋ ፡ ያገኛል ፡ ብለህ ፡ አታመስግነው ።

ወውእቱ ፡ በእንተ ፡ ሕሊናት ።

ይኸውም ፡ አሳብ ፡ ስለ ፡ በዛበት ፡ ነው ።

ዘውእቶሙ ፡ ሰሚዕ ።

ልስማ ፡ ልስማ ፡ ማለት ።

ወከሢተ ፡ አፍ ።

ልናገር ፡ ልናገር ፡ ማለት ።

ወሕፀፀ ፡ ትእግሥት ።

ትዕግሥት ፡ ማጣት ። አንድም ፡ በዓትን ፡ ጥሎ ፡ መውጣት ።

ወድፍረተ ፡ አዕይንት ።

ልይ ፡ ልይ ፡ ማለት ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፪ ።

ወሶበ ፡ ወሰንከ ፡ ለነፍስከ ፡ ሥርዓተ ፡ ዘይደሉ ፡ ለምሕረት ፡ አልምዳ ፡ ለነፍስከ ።

እየመጸወትሁ ፡ እኖራለሁ ፡ ብትል ፡ ሰውነትህን ፡ አለመለያየትን ፡ አስለምዳት ።

ከመ ፡ ኢትኅሥሥ ፡ ርትዐ ፡ ውስተ ፡ ክልዕ ፡ እምግባራት ።

ከለመለያየት ወደመለያየት ፡ ሂደህ ። አንድም ፡ ከወንጌል ፡ ወደ ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ ሂደህ ፡ አድልዎን ፡ እንዳትሻ ።

